# በቀበሌ መታወቂያ ላይ ብሔር/ብሔረሰብ እንዲጠቀስ ለምን ተፈለገ? የህጋዊነቱስ ጉዳይ?

**ታህሳስ 1/2010 ዓ.ም**

**ሲሳይ መንግስቴ አዲሱ**

መስከረም 15/2010 ዓ.ም የእንግሊዙ ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬሽን (BBC) በአማርኛ ዜና ትንታኔው ላይ እንዳቀረበው የምስል መግለጫ መታወቂያ ላይ" ብሔር" የሚለውን ለማስተካከል ረጅም ጉዞ የተጓዘው ያሬድ ሹመቴ በሚል ርዕስ ኢትዮጵያዊው የፊልም ባለሞያ ያሬድ ሹመቴ በቀበሌ መታወቂያ ላይ ብሐየር/ብሐየረሰብ የሚለውን መጠይቅ ለማስቀረት ያደረገውን ጥረት በሰፊው አትቷል።

እንደ BBC ዘገባ ከሆነ የፊልም ባለሞያው ያሬድ ሹመቴ ይህንን ጥረቱን ከስምንት ወራት በፊት የጀመረው ቢሆንም በአስቸኳይ ጊዜ አዋጁ ምክንያት ለተወሰነ ጊዜ አቋርጦት ከቆየ በኋላ አሁን ግን አቤቱታውን ለፌዴሬሽን ምክር ቤት ለማቅረብ በዝግጅት ላይ መሆኑንም ገልጧል። ይህም በእኔ እምነት ከአንድ ያገባኛል ከሚል ኢትዮፒያዊ ዜጋ የሚጠበቅ ተግባር በመሆኑ ያሬድ ሹመቴ ጥረቱን አጠናክሮ እንዲቀጥል ማበረታታት ብቻ ሳይሆን ከጎኑ ተሰልፈን ልናግዘውም ይገባናል የሚለው መልዕክቴ በቅድሚያ ይድረስልኝ እላለሁ።

ይህን የምልበት ምክንያት የብሔር መጠይቅ በቀበሌ መታወቂያ ላይ መኖር አለመኖር ጋር ተያይዞ እኔም በውስጤ ይብላላ የነበረ ሀሳብን ያሬድ ሹመቴ በግልጽና በድፍረት አንስቶ ለመገናኛ ብዙሀን እንዲደርስ ማድረጉ በእጅጉ ደስ ስላሰኘኝ የእሱንም ሆነ የእኔን አተያይ ለተደራሲያን በማጋራት ይዞት የተነሳው ሀሳብ የውይይት ርዕሰ ጉዳይ እንዲሆን ፈግሁና ቀጥሎ በሚገኙት አንቀፆች ላይ እንደ አስፈላጊነቱ በ BBC ድረገጽ ላይ የሰፈረውን የያሬድ ሹመቴን አስተያየት በማጣቀስ ጭምር እኔም የተወሰነ ነገር ማለትን ፈለግሁ።

እርግጥ ነው ባለፉት 26 አመታት ኢትዮጵያ ውስጥ ከቀድሞው በተለየ ሁኔታ በጥቅሉ የኢትዮጵያ ህዝብ የሚለው አባባል ቀርቶ ብሔር፣ ብሔረሰብና ህዝብ ብሎ መጥራት በእጅጉ እየተለመደ መጥቷል፣ በሽግግር ወቅት ቻርተር እና በአዋጅ ቁጥር 7/1984 ላይ የተጀመረው የብሔር-ብሔረሰብ ጽንሰ ሀሳብ ህዳር 29/1987 ዓ.ም ጸድቆ ከነሀሴ 15/1987 ዓ.ም ጀምሮ ስራ ላይ በዋለው የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ህገ-መንግስት ከመግቢያው ጀመሮ እኛ የኢትዮጵያ ብሔሮች፣ ሔረሰበቦችና ህዝቦች በማለት የብሔር-ብሔረሰብን ጉዳይ ትልቅ ቦታ ሰጥቶት እናገኛለን።

ህገ-መንግስቱ በዚህ ሳይወሰን በአንቀጽ 8 ላይ ደግሞ ልኣላዊ ስልጣን የብሔሮች፣ ሔረሰበቦችና ህዝቦች ነው በማለት ከመደንገጉም በላይ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ህዝቦች የራሳቸውን እድል በራሳቸው የወሰን እስከመገንጠል መብት እንዳላቸው በአንቀጽ 39 ንዑስ ቁጥር 1 ላይ አረጋግጧል። ከዛም አልፎ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ህዝቦች ማለት ምን ማለት እንደሆነም በዚሁ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 5 ላይ በግለጽ ለማመላከት ሞክሯል።

ይሁን እንጂ የህገ-ምንግስቱ ትርጉም ለመብት አጠቃቀም አመቺነት ሲባል የተደረገ እንጂ ሶስቱም መጠሪያዎች ተመሳሳይ የሆነ ትርጉም ስላላቸውና በይዘትም ሆነ በቅርጽ አንድ ሆነው በመገኘታቸው እንዳልሆነ ልብ ሊባል ይገባል። ይህን መሰረተ ሀሳብ ተከትሎም የክልል መስተዳድሮች በአብዛኛው በቋንቋ ላይ እንዲመሰረቱ ተደርጓል፣ በዚህም መሰረት ትክክል ነው ለማለት ባያስደፍርም ብሔራዊ ክልሎች በሚያዘጋጁት የቀበሌ መታወቂያ ወረቀት ላይ ብሔር ወይም ብሔረሰብ የሚል መጠይቅ ማካተታቸው/ማስፈራቸው ብዙም አነጋጋሪ ጉዳይ ባልሆነ ነበር።

ምክንያቱም ቀደም ብለን ለመግለጽ እንደሞከርነው የክልል መስተዳድሮቹ አፈጣጠርና አደረጃጀት በራሱ የዚህ አይነት ቅኝት እንዲኖራቸው ሊያደርግ ስለሚችል ነው። በሌላ አነጋገር ብሔርን ወይም ብሔረሰብን በቀበሌ መታወቂያ ላይ መጥቀስ መንግሥት ከዘረጋውና በዋነኛነት ማንነትን መሰረት አድርጎ ከተቋቋመው የፌዴራል ስርአት ጋር በእጅጉ የተቆራኘ በመሆኑ ላለፉት 26 ዓመታት ሲያነታሪክ ቢቆይም አሁንም ጥያቄው እንደ አዲስ የሚነሳበት አጋጣሚ መፈጠሩን በመግቢያየ ላይ ያነሳሁት የፊልም ባለሞያው ያሬድ ሹመቴ ህጉን ተከትሎ አቤቱታውን ለአስተዳደር አካላት ብቻ ሳይሆኑ ለፍርድ ቤቶችም በማቅረብ ጭምር ይህን ሁኔታ እንዲያስተካክሉ ያደረገው ጥረት አንድ ማሳያ ተደርጎ ሊወሰድ ይችላል።

ሆኖም በዚህ ረገድ እጅግ ግራ አጋቢ የሚሆነው ጉዳይ የአዲስ አበባና የድሬዳዋ ከተማ አስተዳደሮች በሚያዘጋጁት የመታወቂያ ወረቀት ላይ ብሔር የሚል መጠይቅ መካተቱ/መስፈሩ ነው። ይህም ሁኔታ በአንድ በኩል በጥቅሉ ብሔር፣ ብሔረሰብና ህዝብ እየተባለ በሚጠራበትና የትኛው ማህበረሰብ ብሔር፣ የትኛው የህብረተሰብ ክፍል ደግሞ ብሔረሰብ ተብሎ በግልጽ ባልተለየበተ ሁኔታ በየትኛውም ክልል በአጠቃላይና በአዲስ አበባና ድሬዳዋ ከተማ አስተዳደሮች ውስጥ በተለይ የሚዘጋጅ መታወቂያ ላይ ብሔር የሚል መጠይቅ ማካተት ብዙዎቹን ኢትዮጵያዊያን ዜጎች ግራ የሚያጋባ ጉዳይ ሆኗል።

ይህ አጠቃላይ ሁኔታ እንደተጠበቀ ሆኖ ብሔር ማለት አገር ማለት ነው ብለው በጽኑ ለሚያምኑና ለሚያስቡ ወገኖች ደግሞ እስካሁንም ድረስ በምንም መልኩ ሊዋጥ የሚችል አባባል ሆኖ አልተገኘም። ከሁሉም በላይ ግን ከተለያዩ ብሔር - ብሔረሰቦች የተወለዱ ዜጎችና በሚሊዮን የሚቆጠሩ የከተማ ነዋሪዎች አንድ ብሔር ወይም ብሔረሰብ ብቻ ለይተው በቀበሌ መታወቂያ ላይም ሆነ በህዝብና ቤቶች ቆጠራ ሰነድ ላይ እንዲሞሉ መገደዳቸው በምንም መልኩ ምክንያታዊ ብቻ ሳይሆን ህጋዊም አይደለም።

እንዲሁም ቀጥለን ዘርዘር አድርገን ለመግለጽ እንደምንሞክረው የተለየ ማንነት አለን እያሉ ነገር ግን እስካሁንም ድረስ በመንግስት እውቅና ያላገኙ የህብረተሰብ ክፍሎች ምን ብለው እንደሚሞሉ ይበልጥ ግራ መጋባታቸው ነባራዊ ሀቅ መሆኑ አሌ የሚባል ጉዳይ አይደለም። ለዚህም ይመስላል የፊልም ባለሙያው ያሬድ ሹመቴ ይህንን የተዛባ ሁኔታ ለማስቀረት ብዙ ርቀት ለመጓዝ የሞከረውና "ብሔር ለሚለው ሀሳብ ለኔ ኢትዮጵያ የምትለው ትበቃኛለች።" በማለትም የተቃውሞ ሀሳቡን የሚገልጸው።

ባለፉት ሁለትና ሶስት ዓመታት በተለያዩ ክልሎች ውስጥ እየተስተዋሉ ባሉት ብሔርን መሰረት ያደረጉ ግጭቶችና ውጥረቶች ምክንያት መታወቂያው ላይ ብሔር ብሎ መስፈሩን ያሬድ በፍጹም ሊቀበለው እንዳልቻለ ለBBC ገልጧል። ሀሳቡን አጠናክሮ በመቀጠልም "በብሔር ምክንያት የወዳጆች ግንኙነት እየተበላሸ፤ ለብዙዎች በሰላም ከሚኖሩበት ቦታ ለመፈናቀል ምክንያት በመሆኑ አደገኛነቱ እየጎላ መጥቷል።" በማለት የሚናገረው ያሬድ ሹመቴ ይኸ ጥረቱ ለራሱ ብቻ ሳይሆን ብሔርን እንደ ማንነት መገለጫ አድርገው መውሰድን መተው ለሚፈልጉ ዜጎች ሁሉ መነሳሳትን ሊፈጥር እንደሚችል ያምናል።

እንደ ያሬድም ሆነ ሌሎች በርካታ ኢትዮጵያዊያን እምነት ባለፉት ሀያ ስድስት አመታት እየታየ ያለው ብሔርን መሰረት ያደረጉ ቡድኖች መጠናከር የኢትዮጵያ ብሔርተኝነትን በእጅጉ አዳክሟል፤ በዚህም ምክንያት ኢትዮጵያዊ ማንነትን ከማቀንቀን ይልቅ ብሔር/ብሔረሰብ ላይ ማተኮር የበለጠ ጎልቶ ይታያል፣ ይህም በመሆኑ አንድነታችን ከመቼውም ጊዜ በላይ አደጋ ላይ ወድቋል። ሆኖም "ብሔራቸውን በመጥቀስ አማራ፣ ኦሮሞ፣ ትግራይ ተብሎ እንዲፃፍላቸው የሚፈልጉት ምርጫቸው ይጠበቅ፤ ማንም ኢትዮጵያዊ ላይ ብሔር እንዳይፃፍ የሚል ጥያቄ የለኝም። ለኔ ግን የማይገልፀኝን ነገር፣ በህገ - መንግሥቱም የማልገደድበትን ማንነት ሊፃፍብኝ አይገባም።

ስለሆነም የኔም ጥያቄ ይመለስ መብቴም አይከልከል ነው እያልኩ ያለሁት።" ይላል የፊልም ባለሞያው ያሬድ ሹመቴ በግሉ በዚህች አገር ላይ እንዲሆን የሚፈልገውን ሀሳብ ይበልጥ ሲያብራራ። ይህንን እምነቱን መነሻ በማድረግም ከላይ እንደተገለጸው ከስምንት

ወራት በፊት ለሚመለከታቸው የመንግስት አካላት ያቀረበው ጥያቄ በወቅቱ ተቀባይነት ባለማግኘቱ ወደ ወረዳው ሥራ አስፈፃሚ እንደተመራለት ይገልጻል።

በማህበራዊ ድረ-ገፁ ላይ በግልጽ እንዳሰፈረውም ብዙዎች የጉዳዩን አስፈላጊነት እንዳልተረዱት ከመግለጹም በላይ "ብሔርህ በእናትህ ተፅፎ ነው እንዴ?" እና "አንድ ሰው ብሔር ሳይል እንዴት ዜጋ ሊሆን ይቻላል? ስለሆነም በመታወቂያ ላይ ብሔር የሚለው መጠይቅ መካተቱ የግድ ነው።" የሚሉ ጥያቄ አዘል አስተያየቶች የቀረቡለት መሆኑ ብቻ ሳይሆን መልሳቸውም "መመሪያው አይፈቅድም!" የሚል እንደሆነም ያሰምርበታል።

ከላይ ለተጠቀሱት አስተዳደራዊ መዋቅሮች ያቀረበው ጥያቄ ምላሽ ባለማግኘቱ ጉዳዩን ወደ ፍርድ ቤት እንደወሰደውና ፍርድ ቤቶችም ይኸ ጉዳይ የህገ-መንግስት ትርጉም ጥያቄ የሚያስነሳ በመሆኑ እኛን ሳይሆን የፌዴሬሽን ምክር ቤትን ነው የሚመለከተው ብለው እንደመለሱት ያስረዳል። እናም ስራ ላይ የሚገኘው መመሪያ አንድም በአውጭው አካል በራሱ አሊያም ከሱ በላይ በሆነው ህግ አውጭ ተቋም ተስተካክሎ ህጋዊ መልክ እንዲይዝና የሁሉንም ዜጎች ፍላጎት በተለይም ከተለያዩ ብሔር-ብሔረሰቦች የተወለዱና በእርግጠኝነት ይኼ ነው ብሔሬ ወይም ብሔረሰቤ ማለት ለማይችሉ ወገኖች ምቹ ሁኔታ ይፈጠር ዘንድ ሁላችንም በያገባናል ስሜት ተነሳስተን መታገል ያለብን ይመስለኛል።

ከዛም አልፎ የራሳችን የሆነ ማንነት ስላለን የዚህኛው ወይም የዚያኛው ብሔር/ብሔረሰብ አካል ነን ብለን መሙላት አንፈልግም ለሚሉ የህብረተሰብ ክፍሎችም ሁኔታው ይበልጥ አስቸጋሪ በመሆኑ የብሔር/ብሔረሰብ ጉዳይ መታወቂያ ላይ መስፈሩ እንዲቀር መጠየቁ በእኔ እምነት ምክንያታዊ ብቻ ሳይሆን ህጋዊም ነው።

ይኸ ጉዳይ በመታወቂያ ላይ ብቻ ተወስኖ መቅረት እንደሌለበትና በዚህ አጋጣሚ በቅርቡ በሚካሄደው የህዝብና ቤቶች ቆጠራ ጊዜም ግምት ውስጥ እንዲገባ ከወዲሁ ማስገንዘቡ ተገቢ ሳይሆን አይቀርም። ምክንያቱም ቀደም ባለው ዘመን ጀምሮ በሀገራችን የተለያዩ ብሔሮችና ብሔረሰቦች መኖራቸው የሚታወቅ ቢሆንምና ይኸው እውነታም በኢትዮጵያዊያን ጸሐፍት በተዘጋጁ ድርሳናት ላይም ሆነ በውጭ አገር ተጓዦችና ተመራማሪዎች አማካኝነት የብዙዎቹ ስምና ማንነት እንደሁኔታው ቢዘረዘርም እስካሁን ድረስ ትክክለኛ ቁጥራቸውም ሆነ በመካከላቸው ያለው ልዩነት አለመታወቁ ይበልጥ ግራ አጋቢ ነውና። በዚህ ረገድ ፈር ቀዳጅ የሆነ ስራ የተሰራው በደርግ ጊዜ ተቋቁሞ በነበረው የኢትዮጵያ ብሔረሰቦች ጥናት ተቋም አማካኝነት በተካሄደው ሁለገብ ጥናት ሲሆን በዚህ ጥናት ውጤት መሰረት የኢትዮጵያ ብሔር-ብሔረሰቦች ቁጥር 89 እንደሆነ መግለጹ ይታወቃል።

ይህም ሆኖ ጥናቱ የ89 ብሔረሰቦችን ስም ዝርዝር ቢያቀርብም ኢትዮጵያ ውስጥ የሚገኙት ብሔረሰቦች እነዚህ ብቻ አለመሆናቸውንም ጥናቱ እንደመንገዱን ሳይጠቁም አላለፈም። ከእነዚህ በዝርዝር ከቀረቡት 89 ብሔረሰቦች መካከል ታሪካቸው በአጭሩም ቢሆን ተተንትኖ የተጻፈው ግን የ75ቱ ብቻ መሆኑን ዶ/ር ፍስሀ አስፋው የኢትዮጵያ ብሔረሰቦችን የሚገልጥ ጥናታዊ መዘክር፣ ብዛት፣ ምንነት፣ ማንነትና አሰፋፈር በሚል ርዕስ አዘጋጅተው ታህሳስ 2008 አሳትመው ገበያ ላይ ባዋሉት መጽሀፍ ከገጽ 21-136 ላይ በግልጽ አስፍረውት እናገኛለን።

ይሁን እንጂ በመንግስት ደረጃ ለእነዚህ ብሔረሰቦች የሚሰጠው እውቅና እንደየጊዜው ሁኔታ ልዩነት እንደሚታዩበት መረጃዎች ይጠቁማሉ። ለምሳሌ በ1984 ዓ.ም. የሽግግር መንግስቱ የክልሎችን አደረጃጀትና አስተዳደራዊ መዋቅር ለመወሰን ባወጣው አዋጅ ቁጥር 7/1984 መሰረት የብሔር-ብሔረሰቦች ብዛት 63 ብቻ የነበረ ሲሆን በ1987 ዓ.ም

በተካሄደው የሕዝብና ቤቶች ቆጠራ ውጤት መሰረት በኢትዮጵያ የሚገኙት ብሔር-ብሐየረሰቦች 84 እንደሆኑ ቢገለጹም በመንግስት እውቅና አግኝተው በፌደሬሽን ምክር ቤት መቀመጫ እንዲኖራቸው የተደረጉት ግን 67 ብቻ ነበሩ።

ከዛም ባሻገር በርካታ የኢትዮጵያ ብሔር-ብሔረሰብ ህዝቦች በየጊዜው በሚያቀርቡት የማንነት ይታወቅልን ጥያቄ ሳቢያ ከ1993 ዓ.ም ጀምሮ በብሔረሰቦች የሚያዘው የፌደሬሽን ምክር ቤት መቀመጫ እየጨመረ በመሄዱ በአሁኑ ወቅት 77 ብሔር-ብሔረሰቦች ውክልና ያገኙበት ሁኔታ ተፈጥሯል። እንዲሁም በ1999 ዓ.ም. በተካሄደው የሕዝብና ቤቶች ቆጠራ ውጤት መሰረት የብሔረሰቦቹ ቁጥር በአንድ ጨምሮ ወደ 85 ያደገ ቢመስልም በ1987 ዓ.ም ተካሂዶ በነበረው የህዝብና ቤቶች ቆጠራ ከተጠቀሱት ነባር ብሔረሰቦች ውስጥ አምስቱ ሳይካተቱ እንዲቀሩ ተደርጎ ሌሎች ስድስት በአዲስ መልክ መጨመራቸውም ይታወቃል።

ይህም ማለት ባለፋት አስር አመታት አምስት ብሐየረሰቦች "ሞተው" ስድስት ብሔረሰቦች ደግሞ "ተወልደዋል" እንደማለት ነው። ነገር ግን ሞተዋል ከተባሉት ብሔረሰቦች መካከል የቅማንት ብሔረሰብ አንሰራርቶ ባካሄደው መራር ተጋድሎ ከሁለት አመት በፊት በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት እውቅና አግኝቶ እንደ አንድ ብሔረሰብ ስለተመዘገበ በፌዴሬሽን ም/ቤትም ውክልና ማግኘቱ ይታወቃል።

ይህም ሆኖ ከፍ ብሎ ከተመጠው የብሔረሰቦች ቁጥር አንጻር አሁንም በደቡብና በኦሮሚያ ብሐየራዊ ክልሎች ውስጥ የሚገኙ ከአስር በላይ የሚሆኑ ብሔረሰቦች በየክልሎቹም ሆነ በፌዴራል መንግስት እውቅና ባለማግኘታቸው ምክንያት በፌዴሬሽን ምክር ቤት ውክልና ሳያገኙ መቅረታቸውን መገንዘብ እንችላለን።

በፌዴሬሽን ምክር ቤት ሊኖራቸው የሚገባውን ውክልና አለማግኘታቸው ጽድቁ ቀርቶ ቢያሰኝም እንኳ እነዚህ የህብረተሰብ ክፍሎች ብሔር/ብሔረሰብ ተብሎ በሚጠየቀው መታወቂያ ላይ ምን ብለው እንዲሞሉ ነው የሚጠበቀው? ለዚህም ነው ጉዳዩ እንዲሁ ተራ ቃል በመታወቂያ ላይ የመቀመጥ ያለመቀመጥ ሁኔታ ስልላሆነ ትኩረት ሊሰጠው ይገባል እንድንል የምንገደደው።